## ሮሃ ግሩፕ በ300 ሚሊዮን ዶላር የሜዲካል ካምፓስ በአዲስ አበባ ሊገነባ ነው

## *ሜዲካል ካምፓሱ በኢትዮጵያ የሜዲካል ቱሪዝም ስበት ማዕከል ይሆናል*

**ሚያዝያ 2 2013 ፤** ሮሃ ሜዲካል ካምፓስ ኃ/የተ/የግ/ማ 300 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ የተቀናጀ የጤና አገልግሎት ካምፓስ ግንባታ ዶ/ር አብይ አሕመድ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ፣ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ የአዲስ አበባ ምክትል ከንቲባ ፣ ወ/ሮ አለምፀሀይ ጳውሎስ የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ፣ ብሩክስ ዋሽንግተን የሮሃ ግሩፕ መስራች እና የሮሃ ሜዲካል ካምፓስ ዋና ስራ አስፈጻሚ እንዲሁም የአሜሪካ ኤምባሲ ተወካዮች በተገኙበት ይፋ አደረገ።

ሮሃ ሜዲካል ካምፓስ የንቅላ ተከላ እና ካንሰር ሕክምናን ጨምሮ በዘመናዊ ሕክምና እና ቀዶ ጥገና ስፔሻላይዝ ያደረጉ 1,100 (አንድ ሺ አንድ መቶ) አልጋዎችን የያዙ 5 (አምስት) ሆስፒታሎች ይኖሩታል። ካምፓሱ በአመት ከ 100,000 (መቶ ሺ) በላይ ለሚሆኑ ታካሚዎች ጥራት ያለው እና ተመጣጣኝ የጤና እንክብካቤ የሚሰጥ ይሆናል። ከአልጋዎቹ ውስጥ 10 በመቶዎቹ ከመንግስት የሪፈራል ሆስፒታሎች ለሚመጡ ታካሚዎች አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው።

ሮሃ ሜዲካል ካምፓስ ፈዋሽ ከባቢ ያለው እና ለሕዝብ ክፍት በሆነ ፓርክ ውስጥ የሚያርፍ ይሆናል። ፓርኩ የእግር መጓጉ መንገዶች ፣ መመገቢያ ስፍራዎች እና የተለያዩ መዝናኛ አገልግሎቶችን በአዳሽ እና ተፈጥሮአዊ ከባቢ ሁኔታ ውስጥ ይሰጣል።

ካምፓሱ ስልጠናዎች እና ትምህርት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን ሲጠናቀቅ ከ 5,000 (አምስት ሺ) በላይ የስራ እድሎችን ይፈጥራል። ካምፓሱ የሜዲካል ትምህርት ቤት ፣ የጥናት እና የፈጠራ ማዕከል እና ሲሙሌሽን ተኮር የስልጠና ሴንተር ይኖሩታል።

አገልግሎት መስጠት ሲጀምር ወሳኝ ዲፓርትመንቶቹ ከአለም ዙሪያ በተውጣጡ ቀዳሚ የሕክምና ባለሙያዎች የሚመሩ እና የሚደገፉ ሲሆን በ5 (አምስት) አመት ውስጥ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎች እንዲመራ ታቅዷል።

ግንባታው በሚቀጥሉት ወራት ውስጥ የሚጀመረው የዚህ ካምፓስ አጠቃላይ ግንባታ ምእራፎችን በ5 (አምስት) አመት ውስጥ ለማጠናቀቅ ታቅዷል። ከ5 (አምስቱ) ውስጥ የመጀመሪያው ፤ ሙሉ ቀዶ ጥገና እና ኢንተርናል ሜዲሲንን ጨምሮ የተለያዩ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥ ባለ 350 (ሶስት መቶ ሃምሳ) አልጋ ዘመናዊ ሆስፒታል ነው።

ሮሃ ሜዲካል ካምፓስ ለታካሚዎች ከፍተኛ ጥራት እና ደህንነት ያለው የጤና እንክብካቤ የሚሰጥ ሲሆን አሉ ከተባሉ አለም አቀፍ ተቋማት የእውቅና ሰርቲፊኬት እንደሚያገኝ ይጠበቃል። አጠቃላይ ካምፓሱ አረንጓዴ እና ዘላቂ ሆስፒታል መርሆዎችን በተከተለ መልኩ የሚገነባ ሲሆን የሶላር ፓነል ያካተቱ ጣራዎች ፣ የራሱ የሆነ መልሶ መጠቀሚያ (ሪሳይክሊንግ) እና በአዲስ አበባ ላሉ ሌሎች ሆስፒታሎች ክፍት የሚሆን ውጋጅ (ዌስት) ማኔጅመንት ፋሲሊቲ ያለው ይሆናል።

የሮሃ ግሩፕ መስራች የሆኑት ብሩክስ ዋሽንግተን በዝግጅቱ ላይ "የግል ዘርፉ ጥራት ያለው እና ተመጣጣኝ አገልግሎት በመስጠት የጤና ዘርፉን ክፍተት ለሞሙላት ከፍተኛ ሚና ሊጫወት ይችላል። በዚህም ረገድ ቀዳሚ ሚና በመያዛችን ደስተኞች ነን። ሮሃ ሄልዝ የሚገነባው ሜዲካል ካምፓስ ለአገር ውስጥ ታካሚዎች አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ እና ከሆቴሎች ጋር አብሮ በመስራት ለታካሚዎች የተለዩ ፓኬጆችን በማቅረብ የኢትዮጵያ ሜዲካል ቱሪዝም ስበት ማዕከል ለመሆን ያለመ ነው። ይህም ከኢትዮጵያ ውጭ ለሕክምና የሚሄዱ ታካሚዎችን በመቀነስ ረገድ እና ከሌሎች አገሮችም ታካሚዎች ወደ አገሪቱ እና ወደ ዘመናዊ ማእከላችን እንዲመጡ አስተዋጽኦ ይኖረዋል" ብለዋል።

አክለውም "ለኢትዮጵያ የጤና ዘርፍ እድገት አስተዋጽኦ እንዲኖረን ይህንን አጋጣሚ በማግኘታችን ደስተኞች ነን። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የጤና ሚኒስቴር ከመጀመሪያው ጀምሮ ላደረጉልን ድጋፍ እያመሰገንን በቀጣይም አብረን ለመስራት ያለንን ቁርጠኝነት እንገልጻለን" ብለዋል።

ሮሃ ሜዲካል ካምፓስ የሮሃ ግሩፕ ኢንቨስትመንት የሆነው ሮሃ ሄልዝ አካል ነው። ሮሃ ግሩፕ በኢትዮጵያ ጠንካራ ተሞክሮ ያለው አሜሪካዊ የኢንቨስትመንት ተቋም ነው። ሮሃ ሜዲካል ካምፓስ ግሩፑ የሚያቋቁመው አራተኛ ድርጅት ሲሆን እስከ ዛሬ በኢትዮጵያ ከ 7,500 (ሰባት ሺ አምስት መቶ) በላይ የስራ እድል የፈጠሩ የተለያዩ ድርጅቶች በ 160 (መቶ ስልሳ) ሚሊዮን ዶላር ኢንቨስትመንት አቋቁሟል። ከዚህ በፊት ኢንቨስት ያደረገባቸው ድርጅቶች ጁኒፐር ግላስ የተባለ በደብረ ብርሃን ከተማ ከ 100 (መቶ) ሚሊዮን ጠርሙስ በላይ የሚያምርት ፋብሪካ ፣ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ማሽነሪ ሊዚንግ ድርጅት የሆነው ኢትዮ ሊዚ እና በአዲስ አበባ አይ.ሲ.ቲ ፓርክ ውስጥ ቲር-3 ዘመናዊ የዳታ ሴንተር እየገነባ ያለው ራክሲዮ ዳታ ሴንተር ናቸው።

**<u>ስለ ሮሃ ግሩፕ</u>**

ሮሃ ግሩፕ በአሜሪካ ውስጥ የተቋቋመ ኃላፊነት በተሞላበት መልኩ በአፍሪካ ውስጥ ትርፋማ የሆኑ ድርጅቶች ላይ ኢንቨስት በማድረግ እና በማልማት ላይ የተሰማራ ተቋም ነው። ሮሃ ከጅማሮ አንስቶ አስከ መጨረሻ ድረስ ኢንቨስት በማድረግ አዳዲሰ ድርጅቶችን ያቋቁማል። ተቋሙ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ፣ ቢዝነስ ዘየዎች እና አጋርነቶች በመጠቀም በገበያ ውስጥ ያሉ ክፍተቶችን ወደ አጋጣሚ መቀየር ላይ ያተኩራል። ሮሃ የአፍሪካ ኢኮኖሚ ማንሰራራት የሚሳለጠው በሚቀጥሉት 10 (አስር) አመታት ውስጥ በሚቋቁሙ አዳዲስ ድርጅቶች ላይ የሚመረኮዝ መሆኑን የሚያምን ሲሆን ለዚህም ትራንስፎርሜሽን ቀዳሚ ሚና በመጫወቱ ይኮራል። ሮሃ በአዲስ አበባ ፣ ናይሮቢ ፣ ዱባይ እና ኒው ዮርክ ውስጥ ቢሮዎች ያሉት እና የተባበሩት መንግስታት ኃላፊነት የተሞላበት ኢንቨስትመንት መርሆች (UNPRI) ፈራሚ ነው። ለበለጠ መረጃ www.roha-africa.com ይጎብኙ።





# Launch of Roha Medical Campus: a $300M integrated, multi-facility healthcare development in Addis Ababa

*Roha Medical Campus to be an Ethiopian hub for medical tourism and high-quality care in a beautiful urban park*

**April 10, 2021, Addis Ababa.** Roha Medical Campus PLC today announced the launch of a $300 million integrated healthcare campus in Addis Ababa. The launch took place in the presence of H.E. Dr. Abiy Ahmed, Prime Minister of Ethiopia; H.E. W/ro Adanech Abiebie, Deputy Mayor of Addis Ababa City; H.E. W/ro Alemtsehay Paulos, State Minister of Health of Ethiopia; Mr. Brooks Washington, Founder of Roha Group and CEO of Roha Medical Campus PLC; Representatives of the U.S Embassy along with other invited guests and members of the Media.

Roha Medical Campus will span five hospitals containing over 1,100 beds providing advanced medical and surgical specialties, including organ transplant and oncology, using state-of-the-art technology. The campus will provide high quality and affordable care to well over 100,000 patients annually. Roha Medical Campus has reserved 10% beds for the public sector to ensure the facilities are accessible to as many Ethiopians as possible, regardless of income.

Roha Medical Campus is designed to provide a healing atmosphere in a beautiful urban park that will be open to the public. The park will restore vibrant natural ecosystems and have walking trails, picnic areas, and other recreational activities.

Roha Medical Campus expects to create over 5,000 jobs and is committed to training and education as integral components of its plan. The campus will feature a medical school, research & innovation hub, and training center with simulation-based learning. Roha Medical Campus is committed to medical education, healthcare management training, and capacity building. At launch, leading medical professionals from around the world will support and lead critical departments, with the expectation that medical staff should be fully localized within five years.

Construction on Roha Medical Campus is expected to begin soon, with development of the entire campus occurring over the coming 5 years. The first hospital will be a 350-bed Advanced Multi-Specialty Hospital, with a full range of surgical and internal medicine specialties.

Roha Medical Campus will embody the highest levels of patient safety and quality of health and expects to be accredited by leading international bodies. The entire campus will be built with green, sustainable hospital principles, with solar installed on rooftops, an on-site recycling and waste management facility that will be open to other hospitals in Addis, and safe water treatment.

During the ceremony, Mr. Brooks Washington, Founder of Roha Group and CEO of Roha Medical Campus PLC said, “The private sector can play a major part in enhancing Ethiopia’s health sector by providing high quality and affordable health services for the country and we are excited to play a leading role in that effort. Roha Medical Campus will create an Ethiopian hub for medical tourism, working with Ethiopian Airlines and local hotels to create travel packages specifically for patients. This will contribute to reversing outbound medical tourism and attracting patients from across the region for care at our first-class facilities.”

He further stated that “We are grateful for this opportunity to contribute to Ethiopia’s healthcare development. The Addis Ababa City Administration and Ministry of Health have been very supportive, and we look forward to continuing to work with them to realize this exciting project.”

Roha Medical Campus is part of the Roha Health platform launched by Roha Group. Roha Group is a US-based investment company with a strong track record of building businesses in Ethiopia. This is the fourth company Roha Group has built in Ethiopia, with total investments of over $160 million in the country over the past few years. Through their initiatives, they have supported the creation of over 7,500 jobs in Ethiopia. Roha’s Ethiopia portfolio includes: Juniper Glass, a $100M+ glass bottle manufacturing facility in Debre Birhan; Ethio Lease, which is Ethiopia’s first private equipment leasing company and has already written over 100 leases providing liquidity and critical equipment to the agriculture, construction, and medical sectors in Ethiopia; and Raxio Data Centre which is building Ethiopia’s first Tier-III, carrier neutral data center in the ICT Park in Addis Ababa.

**About Roha Group Inc**

Roha Group Inc. is a US company that responsibly builds profitable businesses in Africa by investing in and developing new companies across the continent. Roha launches new businesses by leading their development from origination to exit, investing growth capital along the way. The firm focuses on opportunities that address latent demand in local markets with world-class technology, business models, and partnerships. Roha believes that Africa’s economic emergence will be fuelled by new companies built over the next decade and is proud to play a leading role in this transformation. Roha has offices in Nairobi, Addis Ababa, Dubai and New York and is a signatory of UNPRI. For further information, please visit www.roha-africa.com.